# ተላላፊ ዕቃዎች ሥነ - ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ

# (ማሻሻያ) ቁጥር 39/2002

ከገቢ፣ ወጪ እና ተላላፊ ዕቃዎች ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ጥፋቶችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚያልቁትን ለመለየትና ውሳኔ መስጠት በማስፈለጉ፣

የቅጣት ውሳኔ የሚሰጥበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የተከሰቱ የአሰራር ችግሮችን መፍትሔ መስጠት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 19(3) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር 39/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

   የተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16/2001 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1) የመመሪያው አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡

❖ "10(3)" የመድረሻ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ በተገለፀው ሁኔታ የደረሱ ዕቃዎችን የትራንዚት ቡድንና የሕግ ማስከበር የስራ ሂደት የስጋት ደረጃው ከፍተኛ መሆኑን በመንገድ ወረቀቱ ላይ በመግለጽ ዕቃው በዝርዝር ተፈትሾ የፍተሻ ውጤቱንና የተወሰደው እርምጃ እንዲገለጽላቸው በማስታወቅ ለዕቃ አወጣጥ እና ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን ያስተላልፋሉ፤ ቡድኖቹም የተገኘውን ውጤት ለትራንዚት ቡድንና ለሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት ለየመቆጣጠሪያ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ፈት ቤት ማሳወቅ እንዲችሉ ያስተላልፋሉ፡፡

2) የመመሪያው አንቀጽ 15 ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

"15. የዕቃ የማስተላለፍ ስራ የሚያስከትለውን ግዴታ ስለመጣስ፡-

1) ማንኛውም ዕቃ የማስተላለፍ ስራ የሚያካሄድ ሰው ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣ ተላላፊ ዕቃ በተፈቀደለት የመተላለፊያ መንገድ ላይ ለሚገኝ ወይም መተላለፉ ለሚያበቃበት የጉምሩክ ጣቢያ በዚህ መመሪያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መድረሱን በወቅቱ ያላሳወቀ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 103 መሠረት፡-

   ሀ) ለመጀመሪያ ጥፋት ብር 5,000

   ለ) ለሁለተኛ ጥፋት ብር 10,000

   ሐ) ለሦስተኛ ጥፋት ብር 20,000

   ይቀጣል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቀጣ ሰው ጥፋቱን ለአራተኛ ጊዜ ፈጽሞ ሲገኝ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ ይገለፃል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው ዕቃ አስተላላፊው ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያልቅለት በፁሑፍ ማመልከቻ ለባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ትራንዚት ቡድን ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ሲሆን ጥያቄ ያላቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ ለሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት ተላልፎ በሕግ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

3) የመመሪያው አንቀጽ 16(1) ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

"16(1) ማንኛውም የማጓጓዣ ኃላፊ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲጠጋ ካደረገ ወይም ከተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ዘግይቶ ከደረሰ (በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንገደኞችን ወይም የዕቃ ጭነት መግለጫ ካለቀረበ) ወይም ማጓጓዣው እንዲንቀሳቀስ በጉምሩክ ከተፈቀደ በኃላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ በአዋጁ አንቀጽ 101 (1) መሠረት፡-

ሀ. ለመጀመሪያ ጥፋት ብር 2,000

ለ. ለሁለተኛ ጥፋት ብር 3,000

ሐ. ለሦስተኛ ጥፋት ብር 5,000

ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚሰጠው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው የማጓጓዣ ኃላፊው ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያልቅለት ለባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ትራንዚት ቡድን በፁሑፍ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ሲሆን ጥያቄ ያልቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ ለሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት ተላልፎ በሕግ እንዲታይ ይደረጋል፡፡፡፡

4. የመመሪያው አንቀጽ 16 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (4) የነበሩት ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (5) በሚል ተስተካክለዋል፡፡

5. ከመመሪያው አንቀጽ 17 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 18 ተጨምሯል፡፡

" 18. ውሣኔ ስለመስጠት"

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15(3) እና 16(2) መሠረት የትራንዚት ቡድን ማመልከቻ ሲደርሰው የአመልካቹን የቀድሞ ጥፋት በማጣራት የውሣኔ ሃሳብ በሁለት ቀናት ውስጥ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

2. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በቀረበለት የውሣኔ ሃሳብ ላይ በሁለት የሥራ ቀናት ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

6. የመመሪያው አንቀጽ 18 እስከ 21 የነበሩት በቅደም ተከተል ከአንቀጽ 19 እስከ 22 በሚል ተስተካክለዋል፡፡

3. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ የማሻሻያ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ፍፃሜ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

4. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ------- ቀን 2002 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር